# አባማ ይፈታ

## የታላቁ ሩጫ ተሳታፊዎች

32 ሺህ ህዝብ የተሳተፈበትና ለ8ኛ ጊዜ የተዘጋጀው ታላቁ ሩጫ ከትናንት በስቲያ (እሁድ) ረፋድ ላይ ሲከናወን ከስፖርታዊ ክንውኑ በተጨማሪ ታላቅ የተቃውሞ ጩኸትም ተካሂዶበታል:: ከህፃን እስከ አዋቂ ፆታ ሳይመርጥ የተካሄደውን ይህን ውድድር ዞር ዞር እያልኩ ለመቃኘት ሞክሬ ነበር:: ያልተቋረጠ ጩኸትና የተለያዩ ጥያቄዎች በግጥምና በዜማ መልክ ከተሳታፊዎቹ አንደበት ተደምጧል:: እጅግ በጣም በርካታ ከሚባሉት ውስጥ በጽሁፍ ለመግለፅ አስቸጋሪ የሆኑብኝ ቀንሼ ጥቂቶቹን እንኳን ለመጥቀስ ያህል « በ40 ብራች ነፃነታችን...» «አባማ ይፈታ » ( አባማ ይፈታ የሚሉት ቴዲን ለመግለፅ ታስቦ እንደሆነ ግልጽ ይሁን) ስንዴው ይቅርብ ነዳጁንም ጠጡት ቴዲዬን ግን ፍቱት» .....« የሚሉና ሌሎች ያልጠቀስኳቸው ጠንከር ያሉ ጥያቄዎች በጩኸት ፣ በፉጨትና በዜማ መልክ ከ32ሺ ህዝብ መሀል በህብረት ይወጣ ነበር:: ለ8ኛ ጊዜ የተዘጋጀው ይኸው « ታላቁ ሩጫ» ለተወዳጁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ማስታወሻ እስኪመስል ድረስ ህዝቡ ለቴዲ ያለውን ጥልቅ ፍቅር በአደባባይ አሳይቷል ማለት ይቻላል:: ቴዲ አፍሮ እንደሚታወቀው ላለፉት 7 ወራት በቃሊቲ እስር ቤት ይገኛል:: የፊታችን ህዳር 22 2001 ዓ/ም የመጨረሻ ብይን ለማግኘት ቀጠሮ የተያዘለት ሲሆን የፍርድ ቀኑን በትዕግስትና ፈጹም በተረጋጋ አዕምሮ በመጠባበቅ ላይ እንደሆነ ቤተሰቦቹና ድምጻዊውን ለመጠየቅ ወደ ቃሊቲ ያቀኑ አድናቂዎቹ ይገልጻሉ:: ቁም ነገር ላይና ሐገራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ወጣ ባለ ሁኔታ ሙዚቃዎቹን ለአድማጩ ህብረተሰብ በመልቀቁ ከህዝቡ ልዩ ፍቅር፣ ክብርና ታላቅ ሙገሳን ያተረፈው ቴዲ በህግ ጥላ ስር ሆኖ ፍርዱን በመጠባበቅ ላይ ባለበት ሁኔታ 32ሺ ህዝብ ሩጫውን ችላ በማለት ከአዲሱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ ጋር እያመሳሰለ ስሜቱን ገልጿል:: ልደታ አካባቢ በጥበቃ ላይ የነበረ አንድ የፌዴራል ፖሊስ አባል በህዝቡ ሁኔታ ተገርሞ « የሚሮጡት ለቴዲ ነው እንዴ ? » የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ መስማት ተችሏል:: በተለይ አንዳንድ የሩቻው ተሳፊዎች ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘው የፌደራል ፖሊስ ዋና መ/ቤት ሲደርሱ (በጥበቃ ስራ ላይ የነበሩ በርካታ የፌዴራል ፖሊስ አባላት እንዲሰማሁቸው ይመስላል) ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ የቴዲን ስም ደጋግመው በመጥራት ውዳሴ ሲያቀርቡ ተደምጠዋል:: ይህንን ያስተዋለ አንድ የሩጫው ተሳታፊ «ህዝቡ ለሮጥ ነው የወጣው ወይስ ዴሞክራሲያዊ መብቱንም ለመጠቀም?» ሲል በግርምት አስተያየት ሰጥቷል:: ቴዲ አፍሮ በስሙና በፎቶው ቲሸርቶች፣ ቁልፍ መያዣዎችና ሌሎችም ቁሳቁሶች ተዘጋጅተው በተለያዩ ጊዜ ለገበያ እንደበቁ ይታወቃል:: ሰሞኑን ደግሞ

ከመቼውም ጊዜ በተለየ ሁኔታ ከአዲሱ የአሜሪካ ተመራጭ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ ምስል ጎን በቲ ሸርት ተዘጋጅቶ ከተማ ውስጥ ለገበያ ቀርቧል:: ቴዲ ከመታሰሩ ከጥቂት ቀናት በፊት በሸገር ሬዲዮ ቀርቦ ከጋዜጠኛ መአዛ ጋር ቃለ ምልልስ ባደረገ ጊዜ.... «ሰሞኑን አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ፣ አጼ ኃ/ስላሴ፣ ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያምና ያንተ ፎቶግራፍ ያለበት የቀን መቁጠሪያ ወጥቷል:: የተጠቀሱት የሀገር መሪዎች ናቸው:: አንተ በምን አግባብ እነዚህ መሀል ገባህ ? ፖለቲከኛ ነህ ?» የሚል ጥያቄ ቀርቦለት የሚከተለውን ምላሽ ሰጥቷል:: ..... « ይህንን ነገር እንግዲህ የሰሩት ሰዎች በበለጠ ቢመልሱልሽ ጥሩ ነበር:: ነገር ግን እንደማንኛውም ሰው መንገድ ላይ ሲሸጥ አይቻለሁ:: ሰው ደግሞ ፍቅሩን የሚገልጽበትና አክብሮቱን የሚገልጽበት የራሱ መንገድ አለው:: ስለዚህ እነሱም ስሜታቸውንና የፍቅራቸውን ነገር ነው እንደዛ ያደረጉት....» ብሏል:: ቃሊቲ እየተመላለሱ የሚጠይቁት ቤተሰቦቹንና የቅርብ ጓደኞቹ እንደሚሉት ሞቅ ባለ ፈገግታና በርካታ ቀልዶችን እያወራ ጠያቂዎቹን በማጫወቱ ባለው ውስጣዊ ጥንካሬ 7 ወር ቀርቶ 1 ወር የታሰረ አይመስልም ይላሉ::

# «ታላቁ ሩጫ ... ብሶት መግለጫ»

አቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

ይቺ ህዳር ወር እኮ ቀስ በቀስ በዓመት በዓሎች ተሞልታ ትርፍ ቀን ሊጠፋባት ነው:: «ህዳር አጠና»፣«ታላቁ ሩጫ»፣ «የብሔር ብሄረሰቦች ቀን» አረ ሌሎችም አይጠፉም:: ባለፉት ሰሞናት ማጤሱን እርግፍ አድርጎ ትቶት የነበረው ወዳጄ ከኪሱ እንደዋዛ ሲጋራውን መዘዝ አድርጎ ለኮሰና ጭሱን አንቧለለብኝ::

«የተውከውን ሲጋራ ዛሬ ምን ተገኘ እና አነሳኸው?» አልኩት በተለመደ ትህትና ወዳጄ ጢሱ ወደ ራሱ አይን እንዳይገባ አንድ አይኑን ጨፍኖ «ህዳር አጠና ነው::» አለኝ:: እና በድጋሚ የሲጋራውን ጢስ ወደ እኔ አንቧለለብኝ:: (በልቤ ታድያ የምታጥነው እኛን ነው እንዴ? እያልኩ በአፌ ዝም!)

በየአመቱ ህዳር 12 «በህዳር አጠና» በርካታ የሃገራችን ክፍል ይታጠናል:: ለምን? ታሪኩ በከፊል የሚከተለውን ይመስላል::

በዛ ዘመንም በሃገሪቱ ህመም በረታ በመላው ሃገሪቱም በሽታው እየተላለፈ በርካቶችን ለሞት ዳረገ:: ህፃናት ሽማግሌ ሳይለይ ለህመም እና ሞት የዳረገው ይህ ዘመን ለሀገሪቱ ትልቅ ስጋት ሆነ:: ምን ይደረግ ሲሉ ሊቃውንት መከሩ:: መከሩ እና ቆሻሻን ሰብስቦ በማቃጠል ህዳርን አጠኑት:: ችግራቸውም ከጭሱ ጋር አብሮ በነነ:: (አንዳንዶች አሁንም ቢሆን ያሉብንን ችግሮች ለማቃለል ብቸኛው መፍትሔ ይኸው ሳይሆን አይቀርም ሲሉ ይደመጣሉ ለምሳሌ እንደ ኑሮ ውድነት፣እንደ መልካም አስተዳደር እጦት፣ እንደ ሙስና የመሳሰሉት ህዳር ሲታጠን ይጠፋሉ የሚል እምነት በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ አለ:: ለምሳሌ ያ ወዳጄ የሲጋራውን ጢስ ወደ እኔ ያቦነነው ችግሬ አንተ ነህ ሊለኝ ፈልጎ ነው:: ምን አደረኩት? ምንም:: ከመምከር በስተቀረ ምን የማድረግ አቅም አለኝ:: እርግጥ ነው ከፀሀዩ መንግስታችን ጋር ሰም እና ወርቅ ሁን ብዬ መክሬዋለሁ፣ እርግጥ ነው «የኑሮ ውድነቱ ጉንፋን እንጂ ደም ብዛት አይደለም እና አለቅጥ አታማር» ብዬዋለሁኝ:: በቅንፍ ውስጥ ቅንፍ ከተቻለ (እውነት ግን ይሄ የኑሮ ውድነት ሰዎቹ ጉንፋን ነው ብለውን እኛም ለስንቱ ተናግረን ስናበቃ ምነው አለቅጥ በረታሳ? ቃል አባይ ሆንን እኮ!))

የሆነ ሆኖ ከዛን ግዜም ጀምሮ ይቺን ቀን ለማክበር በየ አመቱ ህዳር 12 በሀገራችን «ህዳር አጠና» ቆሻሻን በማቃጠል ይከበራል:: በርግጥ በየሚዲያዎቻችን ቆሻሻን የማቃጠል ባህል አካባቢን ይበክላልና አፅዱ እንጂ አታቃጥሉ ተብሏል:: ቢሆንም ግን በርካቶች አሁንም ችግራቸውን ከጢሱ ጋር ለመሸኘት አካባቢያቸውን አፅድተው ቆሻሻንም አቃጥለዋል:: የማፅዳት ስንፍና ያለባቸውም እንደ ወዳጄ ያሉ ሰዎች በሲጋራ ጢስ «ችግር» የሚሉንን እኛን መካሪዎቻቸውን ለማጥፋት ሙከራ አድርገዋል:: የአንዳንድ ግዜ ወጋችንን ለምን በምርቃት አናሞቀውም? (በምርቃና አላልኩም በምርቃት እንጂ ዘንድሮ ሁሉም ህዝብ ቃማቴ በመሆኑ ነው መሰል ነገሮች ሁሉ ከበርጫ ጋር ሲገናኙ ይደመጣል በየ ቦታው የበርጫ ስም እንዲነሳ ግዝት ያለ ይመስላል:: እስቲ በሞቴ ታላቁ ሩጫ ላይ አሁን ስለ ጫት መዝፈን ተገቢ ነው? እግዜር ያሳያችሁ ከተሰራ ግዜ ጀምሮ ተከብሮ እና ታፍሮ የኖረው ቤተ መንግስት ደጃፍ ላይ «መማር ያስከብራል ሀገርን ያኮራል» በሚለው ዜማ «መቃም ያስከብራል መዝፈን ያሳስራል» ሲሉ ብሰማ በእውነት በትውልዱ ላይ አዘንኩኝ ከሁሉ ከሁሉ ነገሩ የተዘፈነው ቤተ መንግስት አካባቢ መሆኑ ደግሞ ይበልጥ አበሳጨኝ:: ማነው ቅሞ የተከበረው? ማነው ዘፍኖ የታሰረው? መልሱልኝ ሯጮች! ብዬ ያን ሁሉ የሩጫ ተሳታፊ ለመምከር እና ለመገሰፅ ፍላጎት የነበረኝ ቢሆንም ሰሚ ባለማግኘቴ በአዘቦቱ ቀን የታላቁ ሩጫ ቲሸርቱን ለብሶ ያገኘሁትን በሙሉ ለመምከር ቀጠሮ ይዣለሁኝ::) ወዳጄ ስለ ህዳር አጠና ጥቅማ ጥቅሞች አውርተን ወሬያችን ይሞቅ ዘንድ ምርቃት እናስከትል ተባብለን ወደ ሌላ ወሬ ገባን ስለ

ታላቁ ሩጫ ቆይተን እናወጋለን አሁን ወደ ምርቃታችንየአባቶቻችን ህዳር አጠና በሽታዎቻችንን ጠራርጎ እንዳጠፋልን የእኛም አጠና አሸባሪዎችን፣ፀረ ልማቶችን፣ ድህነትን እና የኢኮኖሚ እንቅፋቶችን ጠራርጎ ያጥፋልን! አሜን!

ያጥፋልን! ብዬ ስል አንድ ተረት ትዝ አለኝ:: በአንድ ወቅት እግዚአብሔር ወደ አንዱ ሰው ጎራ ብሎ በአባታዊ ትህትና «ልጄ ምን ላድርግልህ?» ብሎ ይጠይቀዋል:: ሰውየውም ከችግሮቹ ብዛት የተነሳ የትኛውን አቃልልኝ ልበለው እያለ ሲያስብ «አይዞህ የጠየከኝን ሁሉ እፈፅምልሃለሁኝ እና የቱን ልናገር ብለህ አታስብ:: ግና ለአንተ የማደርግልህን እጥፉን ለባልንጀራህ አደርግለታለሁኝ::» አለው ሰውየው ለእርሱ ከሚደረገው በዕጥፍ ለወዳጁ ይደረጋል መባሉ አንገበገበው:: እና ስለ ችግሮቹ መፍትሔ ሊጠይቅ የነበረው ሰውዬ «እንግዲያስ ጌታ ሆይ አንድ አይኔን አጥፋልኝ» አለው (የእርሱ አንድ አይን ሲጠፋ የወዳጁ ሁለቱም ይጠፋላ! ለአንተ ከሚደረገው ለወዳጅህ እጥፉን አደርጋለሁኝ አይደል ያለው?»

ይቺን ተረት ያስታወሰችኝ «ያጥፋልን!» የምትለው ምርቃት ብትሆንም ሌላም ጉዳይ ግን አለ:: ነገሩ ወዲህ ነው:: ለመሆኑ በከተማችን ያሉ ጋዜጦች ማዶ ለማዶ ሆኖ መጠዛጠዝ ልብ ብለዋል ወዳጄ? በተለይ «አሉ» በሚባሉ አንጋፋ ሰዎች የሚታተሙ ሁለት ጋዜጦች አሉላችሁ በየ ሳምንቱ አንዱ ስለ አንዱ የሚያወጡት ወሬ የምር ግራ ያጋባል:: አንዳንድ ግዜማ ጋዜጦቹ የግለሰብ ስም እየጠሩ «የእከሌ ሴራ ሲደራ እና ሲበጣጠስ» በሚል አይነት አርዕስት ከሶስት እና አራት በላይ ፅሁፎች በአንድ ግዜ የሚቀርቡበት ግዜ አለ::

በርዕሰ አንቀፅ፣በዜና፣በዳሰሳ፣በወግ፣በአሽሙር ወዘተ ልብ በሉልኝ በሀገሪቱ እና በህዝቧ ዕድገትም ሆነ ችግር ላይ እዚህ ግባ የሚባል ተፅዕኖ ስለሌለው አንድ ግለሰብ ይሔ ሁሉ ሽፋን? ምነው!? ነውር አይደለም እንዴ!?

ባለፈው ሳምንት በዚሁ (ተሳስቼ ስሙን ጠርቼ ጉድ እንዳልሆን) ብቻ በዚሁ በአይጠሬ ጋዜጣ ላይ ስለሌላው አይጠሬ አቻው ክፍል ስምንት ይሁን ዘጠኝ ትረካ ያነበበው አንድ ወዳጄ «በዚህ ጋዜጣ ላይ ኦባማ እና አልሽባብ እንኳን የዚህን ያኽል ሽፋን አላገኙም ስለ አንድ ግለሰብ ይህ ሁሉ ዘገባ ለምን አስፈለገ?» ብሎ ቢጠይቀን ሌላው ወዳጃችን «ባለታሪኩ በሚያሳትመው ጋዜጣ ላይ ደግሞ ስለ እዚህኛው «ጋዜጠኛ» ክፍል አስር ደርሶልሃል» አለን:: የሚገርመው በሁለቱም ጋዜጣ ላይ አንዳቸው ስለ አንዳቸው (አንዱ ሌላውን ሲሳደብ ሌላው ደግም ሰዳቢውን ሳይሆን አሰዳቢውን በመስደብ ነው የሚበቀለው) የሚያወጡት ፅሁፍ ምናባክ የትአባክ አይነት ናቸው:: ታድያ በየ ቦታው

ነገረኛ አይጠፉም አይደል? አንዱ ነገረኛ «ሰዎቹ ሚስት ተናጥቀው ይሆናል!» አለን፡፡ እውነቱን ሳይሆን አይቀርም የኛ ሰው ወይ በሚስቱ ወይ በርስቱ ሲመጡበት ነው የሚያመረው እንጂ ይሄንን ያኽል አንዱ የአንዱ አይን እንዲጠፉ የሚመኙበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ እኒህ ጋዜጠኞች ከሰሙኝ እንካ ሰላምታ በምን ልምታቸውን ትተው እንደ ቀድሟቸው «ስለ ሃገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት መፋጠን እና አንዳንድ እንከኖቹ» እንዲሁም «የኢህአዴግን ጠንካራ ተቃዋሚ ማጣት እና መፍትሔዎቹ» የሚሉ «ጣፋጭ» ዘገባዎቻቸውን እንደሚያሰሙን ተስፋ አደርጋለሁኝ፡፡

አሁን ከላይ ጀመር አድርገን ወደተውነው የታላቁ ሩጫ ጨዋታችን እንመለስ፡፡ ወዳጄ እርስዎ ሮጠዋልን? ድሮ ድሮ ታላቁ ሩጫ ላይ የሮጠ ሰው ስንት ሰዓት ፈጀብህ ነበር የሚባለው፡፡ ዛሬ ግን ስንት መፈክር ፎከርክ ስንት ዘፈን አወጣህ ስንት ግጥም ገጠምክ ነው የሚባለው አሉ፡፡ በበኩሌ ለሰዓት ነው የሮጥኩት፡፡አንዳንድ ወዳጆቼ ግን ለሰዓት ሳይሆን ለመዓት ነው የሮጡት፡፡ እኛ የምናውቀው ኦባማ የአሜሪካን ፕሬዘዳንት ሆኖ መመረጡን ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ መዓተኞች «ኦባማ ይፈታ! ኦባማ ይፈታ!» እያሉ አጥብቀው ሲጠይቁ ነበር፡፡ «ኦባማ ማነው?» አልኩት ከፈካሪዎች አንዱን «ጀግናው ነዋ! አንድነትን፣ፍቅርን፣መተሳሰብን የሚሰብከው ነዋ!» አለኝ፡፡ «ታድያ እርሱ የት ታሰረ፡፡» ብዬ ብጠይቀው ሰውየው ምነው ጌታዬ ንቃት ይጎሎታልሳ! ብሎ ትቶኝ ሔደ፡፡ ትንሽ ሮጥ እንዳልኩኝ ደግሞ አንድ ግጥም ሰማሁኝ «ታላቁ ሩጫ … ብሶት መግለጫ» የምትል፡፡ ለወደፊት እንደሆን እንጂ አሁን ታላቅ የኢኮኖሚ እመርታ እያሳዩ ካሉ ጥቂት ሃገሮች ተርታ መሆናችንን መቼም ህዝቡ ሳይረዳው አይቀርም፡፡ ይህንን እያሰብኩኝ ሌላም ግጥም ሰማሁኝ፡፡ እርሱ ሲያልፍ ሌላም ተተካ አብዛኞቹን ግጥም ከምላቸው ስድብ ብላቸው ይሻለኛል

በዚህ ፅሁፍ የተባለውን ሁሉ መፃፍ ለመንግስቴ ያለኝን ትህትና ያጓድልብኛል፡፡ የሆነ ሆኖ ታላቁ ሩጫ ይህ ህዝብ ስለመንግስቱ በቂ ግንዛቤ እንደሌለው እና ምክር እንደሚያስፈልገው አስገንዝቦኛል፡፡ ስለዚህ በቅርቡ ስብሰባ ሳልጠራ አልቀርም በጆት ከተፈቀደልኝ፡፡

ወዳጄ እዚሁ ላይ እንሰነባበታ፡፡
አማን ያሰንብተን!